# ሰባራ ግጥም ለማስተካከል…

•

ከድሮ ጀምሮ በአገራችን ‘ሰባራ ግጥም’፣ ወይም ‘የመንዝ ግጥም’ እየተባለ ሲነገር የቆየ የግጥም ዘይቤ፣ ወይም አባባል አለ። ለምሳሌ፤

አፋፍ ላፋፍ ስትሄድ
    አግኝቸ ሚዳቋ
በጅራቷ ብይዛት
    ዓይኗ ፍጥጥ አለ።

ግጥሙ ቤት ባይመታም ዜማው፣ ወይም ድምፁ ይገጥማል። የግጥም ድምፅ የሚባለው፤

ተተ ተተ ተተ
 ተተ ተተ ተተ
ተተ ተተ ተተ
 ተተ ተተ ተተ።

የሚለው ነው። በዚህ የግጥም ዜማ መለኪያ ሲታይ በደምብ የሚገጥም ነው። ‘ሚዳቋ’ የሚለው ቃል ግን ‘ፍጥጥ አለ’ ከሚለው ጋር ቤት ስላልመታ ‘ሰባራ ግጥም’ ተባለ። የዚህ ዓይነት ግጥሞች ብዙም ባይሆኑ፣ በመጠኑ ይገኛሉ።

እነዚህን ሰባራ ግጥሞች አንበቦ፣ ወይም ሰምቶ፣ ስቆ፣ ወይም ተገርሞ ያለፈ ብዙ ሰው ሊኖር ይችላል። ሰባራውን መጠገን፣ የተወላገደውን ማቃናት ግን ደስ ይላልና፣ እነዚህን የተሰበሩ፣ ወይም የተወላገዱትን “የመንዝ” ግጥሞች ለማቃናት ያደረግነውን ሙከራ ከዚህ ቀጥሎ እናቀርባለን።

1) አፋፍ ላፋፍ ስትሄድ    አፋፍ ላፋፍ ስትሄድ
    አግኝቸ ሚዳቋ    አግኝቸ ሚዳቋ
በጅራቷ ብይዛት    በጅራቷ ብይዛት
    ዓይኗ ፍጥጥ አለ።    ወገቧ ተንቋቋ።

ወይም፡-

አፋፍ ላፋፍ ስትሄድ    አፋፍ ላፋፍ ልትሄድ
    አግኝቸ ሚዳቋ    ሰፊ ሜዳ እያለ
በጅራቷ ብይዛት    በጅራቷ ብይዛት
    ዓይኗ ፍጥጥ አለ።    ዓይኗ ፍጥጥ አለ።

ከነዚህ ቤት በመምታት ከተስተካከሉት ከሁለቱ አንዱን አንባቢ የወደደወን መርጦ ሊይዝ ይቸላል።

2) እንዲህ መስየህ ብታየኝ ድኻ    እንዲህ መስየህ ብታየኝ ድኻ

የኣማቾቼ ቤት ባለ ጉልላት። የኣማቼ ዝናር መቶ ቀልሃ

- 

ወይም፡-

እንዲህ መስየህ ብታየኝ ድኻ ድኻ ብመስልህ ሳንቲም የሌላት
የኣማቾቼ ቤት ባለ ጉልላት። የኣማቾቼ ቤት ባለ ጉልላት።

3) ዝናብ ዘንቦ፣ ዘንቦ፣ ዝናብ ዘንቦ፣ ዘንቦ፣
ደጁ ጭቃ ነው ደጁ ጭቃ ነው
ያንን እያነሱ ያንን እያነሳህ
ግድግዳውን ልጥፍ። ግድግዳውን ለስነው።

ወይም፡-

ዝናብ ዘንቦ፣ ዘንቦ፣ ዝናብ ዘንቧል ብሎ
ደጁ ጭቃ ነው እጅን ከማጣጠፍ
ያንን እያነሱ ጭቃውን እያነሱ
ግድግዳውን ልጥፍ። ግድግዳውን መለጠፍ።

4) ወይ እዛ ማዶ ወይ እዛ ማዶ
ቃርያ፣ በርበሬ ቃርያ፣ በርበሬ
ባደረ እንጀራ ባደረ እንጀራ
ቢኮሸኩሹት። በሉት መምሬ።

ወይም-

ወይ እዛ ማዶ ቃርያ፣ በርበሬ
ቃርያ፣ በርበሬ ያሳደሩት
ባደረ እንጀራ ጥዋት ተነስተው
ቢኮሸኩሹት። ኮሸኮሹት።

5) አረ ከጓሮ ምን ይንኮሻኮሻል?
ኣባና እማሆይ ሓረግ ይመዝዛሉ።

ይህ በቤት መምታትም ሆነ በግጥም ዜማ እምብዛም ኣይገጥምም። በሁለቱ የግጥም መለኪያዎች “ሰባራ” በመሆኑም በመጨረሻ ኣቅርበነዋል፡-

አረ ከጓሮ ምን ይንኮሻኮል? ኣባ ከጓሮ ምን ያንኮሻኩሻሉ?
ኣባና እማሆይ ሓረግ ይመዝዛሉ። ከእማሆይ ጋራ ሓረግ ይመዝዛሉ።

ገ/ኢ. ጐርፉ።